# በዶክተር ተሰማ ብስራት ሞት መሪሪ ሀዘን ተሰምቶናል

ከኢሮብ መብት ተማጓች ማህበር (መኢተማ)

ለኢሮብ መብት ተማጓች ማህበር (መኢተማ) የዶ/ር ተሰማ ብስራት ዜና ዕረፍት እንደታወቀ የተሰማው መሪር ሃዘን በቃላት ለመግልጽ እጅጉን ይከብዳል። ምክንያቱም ዶ/ር ተሰማ ገና በለጋ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ሶስት ትምህርታቸውን በመከታተል ያሉ ልጆቻቸውን ትተው ማለፋቸው ብቻ ሳይሆን ሀገራችን ኢትዮጵያ ዶ/ር ተሰማ ብስራትን ጨምሮ በርካታ ምሁራን በሁኔታዎችና በየጊዜው የተፈራረቁባት ገዥዎች ግብዝነት ምክንያት ለሀገራቸውና ለህዝባቸው የነበራቸውን በጎ ራእይ ለመተግበር ሳይችሉ ለሕልፈት እየተዳረጉ በመሆናቸው ነው።

መ.ኢ.ተ.ማ ይህንን አጭር መግለጫ የሚያወጣው የዶ/ር ተሰማን የሕይወት ታሪክና ላገራቸው ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ለመዘርዘር ሳይሆን፤ በዶ/ር ተሰማ ብሥራት ሕልፈተ-ሕይወት የተሰማውን ከፍተኛ ሀዘን ለመግለጽ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ባጭሩም ቢሆን እሳቸውን በትክክል ለመግለጽ በሚያስችሉ ተግባሮቻቸው እሳቸውን ለማስታወስና ከሁሉም በላይ ደግሞ ለወደፊቱ የዶ/ር ተሰማም ሆነ የሌሎች የኢሮብ ታዋቂ ምሁራን ታሪክና ያበረቱት/የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በአገባቡ በታሪክ መዝግቦ መያዝ የእያንዳንዳችን የኢሮብ ተወላጆች ተግዳሮት መሆኑን ለማስገንዘብ ነው። ስለሆነም፤ እግረ-መንገዳችን ሁላችን በየ በኩላችን የምሁራኖቻችንና የታዋቂ ሰዎቻችንን ታሪክ የማሰባሰብና የመመዝገብ ሀላፊነት እንድንወስድ አጥብቀን ለማሳሰብም እንገደዳለን።

ዶ/ር ተሰማ ብሥራት በሕይወት ጉዟቸው በትምህርትና በሥራ ልምድ ያካበቱትበን ከፍተኛ ዕውቀትና ተመክሮ ለወገናቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ለማበርከት ዕድል በማጣታቸው እንደተብከነከኑ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩን በርካታ ምሁራን አንዱ ናቸው።

ዶ/ር ተሰማ ብስራት ከኣባታቸው ከልጅ ብሥራት ገብራይና ከናታቸው ከወ/ሮ አምለሱ ሃውኩ በ1935 ዓ.ም. በኢሮብ ወረዳ ልዩ ስሙ ሳራይቲ አራሕ በሚባል መንደር ነበር የተወለዱት። ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰም በወቅቱ በኢሮብ ወረዳ ውስጥ ትምርት ቤት ስላልነበረ ዓጋሜ አውራጃ ዋና ከተማ ወደሆነችው ዓዲግራት ከተማ በመሄድ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በጽንሰታ ለማሪያም የካቶሊክ ትምህርት ቤት ነበር ያጠናቀቁት።

በ1959 ዓ.ም. በጣሊያን ሀገር ከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል ዕድል ካገኙ ተማሪዎች አንዱ በመሆን ወደዛ የተጓዙት ዶ/ር ተሰማ፣ በፊሎዞፊ አንደኛና ሁለተኛ ድግሪያቸውን፣ ከኡርባኒአና ዩንቨርስቲ በማግኘት እንዲሁም ከሮም ስተይት ዩንቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስ በዶክተሬይት ድግሪ በመመረቅ ትምህርታቸውን በስኬት አጠናቀዋል። ዶ/ር ተሰማ ለከፍተኛ ትምህርት ጣልያን አገር በቆዩበት ጊዜ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን በወቅቱ በኤውሮጳ ተስፋፍቶ በነበረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥም ተሳታፊ ነበሩ።

በ1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ለተከሰተው ለውጥ ከፍተኛ ሚና ከነበራቸው ውስጥ ከተማሪው እንቅስቃሴ የተወለዱት ኢህአፓና መኢሶን ዋነኞቹ እንደነበሩ የሚታወቅ ነው። ዶ/ር ተሰማ እንደሌሎቹ የቅርብ ጓደኞቻቸው ቶሎ ብለው የነዚህ ድርጅቶች አባል ሳይሆኑ የቀሩና በተለይ በወቅቱ በጣም ከፍ ብሎ ሲጮህለት የነበረው የብሄር ጥያቄ አንስተው ትግል በጀመሩ ብሄርተኛ ድርጅቶችና ጠባብ አቅዋማቸውን በሚመለከትና፣ የነዚህ ጠባብ ድርጅቶች ዓላማ በሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ ያለው አደጋ አርቆ በማየት የሰላ ሂስ ይሰነዝሩ ከነበሩ ወጣት ምሁራን አንዱ እንደነበሩም ይታወቃል።

ዶ/ር ተሰማ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በስልጣን ላይ የነበረው ወታደራዊ ደርግ ምሁራንን በሞያቸው የመጠቀም ዕድል ሊፈጥር ይችል ይሆናል፣ ውስጥ ሆኖ ስሕተቶችን ለማረም በመርዳት አገርና ህዝብን ለመጥቀም ይቻላል በሚል እምነት ወደ ሀገሬ ገብቼ ይህን ዕድል መሞከር አለብኝ በማለት በሙያቸው ሀገራቸውን ለማገልገል በ1975 ዓ.ም. ጠቅልለው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ገቡ። እንደገቡም ደርግ በሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚንስተር በውጭ ግኑኝነት መምሪያ በምርምር ዘርፍ እንዲሰሩ መደባቸው። በተመደቡበት የሥራ ቦታም በተለያየ የሃላፊነት ደረጃ አገራቸውንና ህዝባቸውን በቅንነትና በታማኝነት አገልግሏል። ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የመሪዎች ጉባኤዎች ሀገራቸውን በመወከል ተሳትፈዋል።

በ1983 ዓ.ም. የወታደራዊ ደርግ ስርዓት አክትሞ ኢ.ህአዴግ በትረስልጣኑን ሲጨብጥ ዶ/ር ተሰማን ያለ ምክንያት ይዞ ለሁለት ዓመታት ያህል በእስርቤት አሰቃይቷቸዋል። በሞያቸው ሀገራቸውን ከማገልገል ውጭ ምንም የሰሩት ወንጀል ስላልተገኘባቸው ግን ከሁለት ዓመታት እስራት፤ ሰቆቃና እንግልት በኋላ ምንም ዓይነት ክስ ሳይመሠረትባቸው፤ የታሰሩበት ምክንያትም ሳይነገራቸው ከእስር ተለቋል። በዚህም ሳያበቃ ከእስር በነጻ እንደተለቀቁ የህወሓት ደጋፊ ወይም አባል በመሆን ህወሓት/ኢ.ህአዴግ በሚመድባቸው የሥራ ገበታ ገብተው እንዲያገለግሉ ጥያቄ ቀርቦላቸው እንደነበረ ለቅርብ ወዳጆቻቸው ተናግረው ነበር። ሆኖም፤ እሳቸው የማላምንበት ዓላማን ማገልገል ስለማልፈቅድ፤ የመጣውን ችግር በራሴ መጋፈጥ እንጂ እንደዛ ዓይነት ህልናየን የሚጎዳ ሥራ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አይደለሁም በማለት ጥያቄውን ሳይቀበሉት ቀርቷል። ይህንንም ለቅርብ ወዳጆቻቸውና ባለመዋሎቻቸውና ጓደኞቻቸው ይናገሩ እንደነበረ የሚመሠክሩ ሰዎች በሕይወት አሉ። ይህ ዓይነቱ እምቢታ የዶ/ር ተሰማን ትክክለኛ ገጸ-ባሕሪ የሚያሳይ ነው። የማያምኑበትን ለመተግበር ፈቃደኛ አለመሆን መለያቸው ነበር። በመሆኑም መሰረታዊ እምነቴን ለጊዚያዊ ጥቅም ለመለወጥ አልሻም በማለት እምቢኝ ማለታቸውንና በዚህ ምክንያትም በሞያቸው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ከማገልገል መታገዳቸው እነዚህ ወዳጆቻቸው ይገልጻሉ።

ይህም፤ ዶ/ር ተሰማ እምነታቸውን በጊዜያዊ ትርፍራፊ ጥቅማጥቅሞች በመደለል ሊለወጡ የማይችሉ፤ በሞራል የታነጹ ሂልናቸውን አታለው ለመኖር የማይከጅሉ ታላቅ የሞራል ሰው እንደነበሩ ያመላክተናል። በዚህ ምክንያትም ከእስር እንደወጡ ሶስት ልጆች ይዘው ለተወሰነ ጊዜ ሥራ አልባ ሆነው እንደቆዩና በኋላ አዲስ አበባ በሚገኘው በካቶሊክ መንፈሳዊ ኮሌጅ በአስተማሪነት ተቀጥረው በፍልስፍና አስተማሪነት በማገልገል ላይ እያሉ ለዓመታት በውስጣቸው አምቀውት ሲኖሩ የነበረው ብስጭትና ጭንቀት ለተለያየ በሽታ ዳርጎዋቸው አንድም ቀን እፎይ ሳይሉ መጋቢት 22 ቀን 2005 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተልይተውናል።

ዶ/ር ተሰማ ትሁት፣ ሰውን አክባሪ፣ ልታይ ልታይ የማይሉ፣ ከፍተኛ የሆነ የማዳመጥ ችሎታ የነበራቸው፣ እምነታቸውን ለምንም ነገር የማይቀይሩ ጽኑ ሰው ነበሩ። መኢ.ተማ ዶ/ር ተሰማና መሰል ምሁራን ሀገራቸውን በሞያቸው ነፃ ሆነው ለማገልገል ብችሉ ሀገራችን ከፍተኛ የዕድገት ልታሳይ ትችል እንደነበረ ያምናል። አለመታደል ሆነና ግን ዶ/ር ተሰማም ሆኑ እሳቸው መሰል ሌሎች ምሁራን ሀገራቸውንና ህዝባቸውን በሞያቸው ያለማንም ጣልቃገብንት ለማገልገል የምችሉበት ዕድል ሳያገኙ፣ የዳበረ ዕውቀታቸውን እንደያዙ፣ አንድም ቀን እፎይ ሳይሉ፣ እንዳዘኑ ከዚህ ዓለም በሞት እየተለዩን መሆኑ እጅግ ያሳዝነናል። ስለሆነም መኢ.ተማ ዶ/ር ተሰማ በዚህ ዓይነት ሁኔታ አንድም ቀን እፎይ ሳይሉ፣ በተመክሮ የዳበረ ከፍተኛ ዕውቀታቸው እንደያዙ ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ከፍተኛ ሃዘን እንደተሰማው እየገለጸ በዚህ አጋጣሚም ለውድ ባለቤታቸው ለወ/ሮ አበባ ዝግታ፣ ለልጆቻቸው፣ ለእህት ወንድሞቻቸው እንዲሁም ለሌሎች የቅርብ ዘመዶቻቸው መጽናናትን ይመኛል።

ነብሳቸውን ይማር፤ ለባለቤታቸውና ለልጆቻቸው እንዲሁም ለመላው ቤተ-ሰቦቻቸው ፅናት እንዲሰጣቸው እንመኛለን።

ሚያዝያ 2005 ዓ.ም